## How a Triad of Forces Emasculated and Undermined the Legitimacy of the Ethiopian Nation-State

**Ghelawdewos Araia, PhD** **February 20, 2021**

This brief article in Amharic will focus on the present Ethiopian crisis (conflict and war) that has effectively but sadly shattered the political, economic, and social fabrics of Ethiopia, and the cause for all these, I argue, are the triad of forces, namely the narrow-minded ethnonationalists, the chauvinist elite and politicians, and the witchcraft politics of a medieval variety that has now become a vogue amongst the ruling clique of the Prosperity Party.

## የሦስትዮሽ  ጸረ– ሕዝብ ኃይሎች፣ የጠባብ አመለካከት፡ የትምክህትና፡ የጠንቋይ ፖለቲካ ኢትዮጵያን እንዴት እንዳተራመሷት

**ገላውዴዎስ ኣርኣያ  ዶ/ር** **የካቲት <u>፩፫</u> <u>፳፻፲፫</u>**

ኢትዮጵያ ታላቅ ሃገር ናት፣ በአፍሪቃ ነፃነቷን ጠብቃ የቆየች ብቸኛ አገር ናት፣ የሰው ዘር መገኛ እና የአፍሪቃ አንድነት ማእከል ለመሆኗም ለግርማ መጎሷ ተጨማሪ ኃይል አልብሷታል ብንል የተጋነነ አይሆንም። ዳሩ ግን ብልህና ልባም ሰው በጠፋበት ዘመንና የውሸት ዶክተሮች በብዙበት ወቅት፡ ኢትዮጵያ በገዛ ልጆቿ ተተራምሳለች፣ ሁሉም አዋቂ፡ ሁሉም ፖለቲከኛ፡ ሁሉም ጋዜጠኛ፡ ሁሉም የሃይማኖት መሪና ሰባኪ በሆነበት ጊዜ እንዴትስ አገሪቷ ከመተራመስ ትዳን! እጅግ በጣም ያሳዝናል።

አሁን በኢትዮጵያ የተከሰተው የፖለቲካና ማህበራዊ ዝቀተት በጣም የተወሳሰበ ከመሆኑም በላይ ለችግሩ መንስኤ ደግሞ ብዙ ምክንያቶችና ኃይሎች ቢሆኑም ቅሉ ለትኩረትና ለትንተና ይመች ዘንድ ግን ይህ ጽሑፍ በሦስትዮሽ ጸረ–ሕዝብ ኃይሎች ብቻ ይወያያል።

**ጠባብ አመለካከት** አድሃሪ ስነልቦናዊ ኃይል ሆኖ ብዙውን ጊዜ የሚመነጨው ከእውነት ማነስና ከድንቁርና ነው። በኔ እይታ ደግሞ የኢትዮጵያ ዋና ጠላት ድህነት ሳይሆን ድንቍርና ነው። የዚሁ ምክንያታዊነት ወይም ርትዓዊነት ግልፅ ማድረግ አስፈላጊ ነው፣ እርግጥ ነው ድህነትም ጠላት ነው፣ ነገር ግን ድንቁርና ከሚያመጣው ችግርና ፈተና ጋር አይመጣጠንም። የነቃና የተደራጀ ሕብረተሰብ በድህነት አረንቋ ቢሰቃይም የተሻለ የአእምሮ ጤንነትና ስነልቦናዊ ስብእና ይኖረዋል፣ በራሱም ይተማመናል፣ ለፍትህና ለእኩልነት ደግሞ ይታገላል። በድንቁርና የታወረ ሕብረተሰብ ግን እንኳንስ ስብእና ኖሮት ለፍትህና ለእኩልነት ሊታገል ይቅርና በተቃራኒው ጸረ–ህዝብና ጸረ–ሃገር ነው የሚሆነው፣ ብዙውን ጊዜ ደግሞ ከእንዲህ ዓይነት ማህበረሰብ የሚፈልቁ ደናቁርት ናቸው የመንግሥት ቅጥረኞች ናቸው የገዛ ራሳቸው ሕዝብ የሚያሰቃዩት፣ አምባገነንና ጨቋኝ መነግሥት ደግሞ ሆን ብሎ ደናቁርትና አድርባይ ግለሰቦችን ነው የሚመለምለውና የሚቀጥረው።

የጠባብ አመለካከት ትሩፋትና እንደምታ ዓይነተኛ ምሳሌ ባለፉት ሦስት ዓመታት በኢትዮጵያ የተከሰተውን የሕዝብ መፈናቀልና የብሔር ብሔረሰቦች አባላት መጠቃትና መገደል ነው። አንድ ደንቆሮ ኢትዮጵያዊ፡ በተለይም የባህልና የኃይማኖት እሴቶችን እርግፍ አድርጎ የጣለ ከሆነ፡ ወንድምና እህት ከሆኑት ኢትዮጵያውያን ከማጥቃት፡ ከመግደል፡ንበረታቸውንና የጸሎት ቤታቸውን ከማቃጠል ወደ ኋላ አይልም። ለዚህም ነው በሺዎች የሚቆጠሩ የትግራይ፡ የኦሮሞ፡ የአማራና ሌሎችም አናሳ ብሔረሰብ አባላት ደማቸው ደመ–ከልብ ሆኖ የቀረው። የጠባብ አመለካከትና የጠባብ ብሔርተኝነት እንደምታ ደግሞ ከዚህ የተለየ ሊሆን አይችልም፣ አንድ ግለሰብ በጠባብ ብሔርተኛነት የተጠመደ ከሆነ፡ የጥላቻ እስረኛም

ስለሚሆን፡ በሌሎች ብሔር ብሔረሰብ አካላዊ ጥቃት ያደርስና እሱም ራሱ የጥላቻ ቁም እሥረኛ ይሆናል፣ ልቡ ይቆስላል፡ መንፈሰ ደካማም ይሆናል፣ ለትልቁ የኢትዮጵያ ማሕበረሰብ ደግሞ የሚያደርገው አንዳችም አስተዋፅኦ አይኖርም። ባጭሩ ጠባብ አመለካከት ያለው ግለሰብ ወይም ስብስብ አሉታዊ ኃይል (negative energy) ስለሆነ ለሕብረተሰቡ አደጋና ኪሳራነትን ያስከትላል።

የጠባብ አመለካከት ሁለተኛ ገፁ **ትምክህተኝነት** ነው። ትምክህተኝነት በሁለት መንገድ ሊገለፅ ይችላል፡- ፩) አንድ ግለሰብ፡ ስብስብ፡ ወይም የአንድ ብሔር አባላት በታሪክ አጋጣሚነት በህብረተሰቡ ዘንድ የበላይነት (የመግሥት ሥልጣን፡ የቋንቋ፡ የኃይማኖት ወዘተ) ከያዙ፡ እነሱ ከሁሉም የህብረተሰቡ አባላት ወይም ብሔሮች የበላይ መሆናቸውን ይሰማቸዋል፣ በሌላ አነጋገር ይህ ክስተት የብሔር/ዘር የበላይነት ስሜት ይባላል፣ ፪) የትምክህተኝነት የበላይነት (superiority complex) ሁለተኛ መገለጫው ደግሞ የውድቀትና የበታችነት ስሜት ለመሸፈን የሚደረግ አመለካከት፡ ጠባይ፡ ወይ አኳሃን (superiority/inferiority complex) ነው።

አንዳንድ ጊዜ ግን ሁለቱ የትምክክህት መገለጫዎች በጣምራነት ሊከሰቱ ይችላሉ፣ ቆየት ብየም አብነት በመስጠት እገልፃቸዋለሁ። ትምክህተኝነት ከብሔር ብሔረሰብ ጭቆና የተያያዘ ሆኖ ጥያቄው ለመጀመርያ ጊዜ ጎልቶ የታየው በኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ በስልሳዎቹና በሰባዎቹ ነው። ጥያቄው መፍትሄ ያገኘ ዘንድ ተማሪዎቹ ከፍተኛ ትግል አካሂደዋል። በቅድመ ግንባር ይታገሉ ከነበሩ መሪዎች ደግሞ ዋለልኝ መኮንን፡ ጥላሁን ግዛው፡ ብርሃነመስቀል ረዳ፡ ኢያሱ አለማየሁ፡ ዘርኡ ክህሸን፡ ዮሐንስ ብርሃነ፡ ብርሃነ ኢያሱ፡ፀጋዬ ገብረመድህን (ደብተራው)፡ ግርማቸው ለማ፡ አብርሃም ገብረእግዚአብሔር፡ ማርታ መብራህቱ፡ ጸሎተ ህዝቅያስ ወዘተ በቅድምያ የሚጠሩ ናቸው። ከሁሉም በላይ ግን ዋለልኝ መኮንን ነበር ግልፅ በሆነ መንገድና በድፍረት ስለ የብሔሮች ጭቆና በኢትዮጵያ ያቀረበው። የተማሪው ንቀናቄ ባጠቃላይ የብሔር ትምክህተኝነት ጠፍቶ የብሔር ብሔረሰብ እኩልነት በፖለቲካ ፕሮግራም ገብቶ፡ በሕግ ተደንግጎ እንዲተገበር ነበር የፈለገው። የተማሪው ፍላጎት በመጠኑም ቢሆን በደርግ ጊዜ በግብር ለመተርጎም ተሞክሮ ነበር። ጥያቄው ሙሉ በሙሉ መልስ ያገኘለት ግን በኢሕአዴግ ጊዜ ነው።

ምናልባት የብሔር ጥያቄ አንዱ ደካማ ጎኑ ለመቀበል ዝግጁ ከሆን ግን ጥያቄው ከመጠን በላይ ተለጥጦ፡ የኋላ ኋላ የመደብ ጥያቄ መሆኑ ተዘንግቶ የአማራን ብሄር በጥቅሉ ጨቋኝ ብሔር አድርጎ ማስቀመጡ ነው። እርግጥ ነው የአማራው የገዢ መደብ የበላይነት እንደነበረው አጠያያቂ ባይሆንም ሰፊው የአማራ ሕዝብ ግን በድህነትና በቸነፈር ይኖር ነበር! በርካታው ደግሞ በደሳሳ ጎጆ ነበር ይኖር የነበረው።

የአማራው የገዢ መደብ የትምክህት ስነልቦና ግን አሁንም ቢሆን አለ፣ በሊህቃኑና ሙሁራኑ በተለይም ባማራ ክልል አስተዳዳሪዎች በሰፊው የሚንጸባረቅ ነው። የአማራ ሕዝብ በልማት እንደይሰማራና ጦርነትን እንደሞያ አድርጎ እንድያይ ያደረጉት እኒህ ትምክህተኞች ናቸው። ያማራን ሕዝብ በእጅጉ በድለውታል፣ ከትግራይ፡ ከኦሮሞ፡ ከበኒሻንጉል ጉሙዝ እንዲጋጭ፡ ቁርሾና ቂም እንዲፈጥር አድርገውታል። ሊሂቃኑ በአገር ውስጥ “ትግራይን እንጨብጣታለን” የሚሉ ሽፍቶችና ትምክህተኞች አፍርተዋል፣ በውጭ አገር ደግሞ እንደ እሳት ተለቪዥን የመሳሰሉ ትምክህተኞችና ጽንፈኛ ፖለቲኮኞች እንዲፈጠሩ አድርገዋል። የእሳት ተለቪዥን ደናቁርት ለብዙ ጊዜ ትግራይን የማጥቃት ከበሮ ሲመቱ ቆይተዋል፣ ቀደም ብለው አምስት በመቶ የትግራይን ሕዝብ በዘጠና አምስት በመቶ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማጥፋት ይቻላል ብለው ሲሞጉቱ ነበር። በቅርብ ጊዜ ደግሞ “ኤርትራ ኢትዮጵያን እንድታግዝና አብረው ትግራይን እንዲወጉ” በግልፅ ተናግረዋል፣ ዓይን ያወጣ ትምክህት ይለዋል ይኸ ነው! ትምክህተኞቹ ግን የሚፈልጉትን ነገር አግኝተዋል ማለት ይቻላል፣ በአብይ አሕመድ ጋባዥነት የኤርትራው ጋኔን ኢሳያስ አፈወርቂ በኢትዮጵያ ጉዳይ ጣልቃ በመግባት የትግራይን ሕዝብ ለመጨፍጨፍ ትልቅ እቅድ አወጣ! በግብርም ተረጎመው፣

የትግራይ ሕዝብ በታሪኩ አይቶት የማያውቅ ጭፍጨፋ ደረሰበት፣ ንብረቱ፡ ቤቱ፡ ማሳው፡ ቤተ ክርስትያኑ፡ ገዳማቱ፡ ትምህርት ቤቱ ሁሉ ወደመበት፣ ተቃጠለበት።

ኢሳያስ አፈወርቂ የትግራይን ሕዝብ ክፉኛ ለመበደል ለምን ተነሳሳ ቢባል ሦስት መልስ ሊኖረው ይችላል፦ ፩) ቂም በቀል ሆኖ፡ የባድመ ጦርነት ሽንፈትና ውርደት ማካካሻ ይሆን ዘንድ በህወሐትና በትግራይ ሕዝብ ላይ ጦርነት ማወጅ ነበረበት፣ ፪) በገዛ ራሱ የማይተማመንና በበታችነት ስነልቦና (inferiority complex) የሚሰቃይ ግለሰብ ነው፣ የኢሳያስ ገጸ ባህርይና ተክለ ሰውነት በኤርትራውነት ተሸፈነ እንጂ የሰውየው የትውልድ ሐረግ ከትግራይ፡ ከተንቤን ነው። የትውልድ ሃረጉን ለመሸፈን ታድያ ትግራይን ማውደም ሕዝቡንም መጨፍጨፍ ነበረበት፣ ፫) ከኢሳያስ ባህርይና ተክለ ሰውነት ጋር የሚቀራረብ ነገር ቢኖር በጀርመን ብሔርተኝነት ሽፋን አንዳንድ አይሁዶች የገዛ ራሳቸውን ዘር ማጥፋት ባደረጉት ትብብር ጋር ይመሳሰላል። እኔ በበኩሌ ግን የኢሳያስ የትውልድ ሐረግ ትርጉም አይሰጠኝም፣ ሰውየው ሁለመናው ኤርትራዊ ነው የሚል እምነት ነው ያለኝ።

በዳያስፖራ ያሉት ትምክህተኞች ደግሞ ለኢትዮጵያ መፍረስ ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል፣ ከነዚህ ትምክህተኞች በርካታዎቹ በአብይ አሕመድ ጋባዥነት የዛሬ ሦስት ዓመት ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው ገብተዋል፣ ለኢትዮጵያ መዳከምና መፈረካከስ ደግሞ ብዙ አስተዋፅኦ አድርገዋል። ነገር ግን አሁንም ቢሆን አያሌ ትምክህተኞች በሰሜን አሜሪካ፡ በአውሮፓና አውስትራልያ ይገኛሉ። ከነዚህ ትምክህተኞች አንዳንዶቹ የራሳቸው ድረገፆች አላቸው፣ ሬዲዮና ተለቪዥን ያላቸውም አሉ፣ ቀደም ብዬ እንደጠቀስኩት የእሳት ተለቪዥን ለአስር ዓመታት ሲደነፉ ከቆዩ በኋላ ገሚሶቹ ተገንጥለው በመውጣት ኢትዮ 360 የሚል ቲቪ መስርተው መንቀሳቀስ ጀመሩ፣ የዓላማ ልዩነት እንዳላቸው ለማሳየት ይሞክሩ እንጂ ያው ናቸው፣ ዞር ነው ያሉት፡ አልሸሹም፣ ጉልቻ ቢቀያየር ወጥ አያጣፍጥም እንደሚባል ሁሉ በውስጥ ድብቅ አላማቸውና ትምክህትነታቸው እንዲሁም በጠባብ አመለካከታቸው ያው ናቸው።

ኢትዮ 360 በቅርብ ጊዜ "የ ዶ/ር ገላውዴዎስ አርአያና የወልቃይት ጉዳይ" በሚል ርእስ ባቀረቡት ፕሮግራም አቅራቢው ወይም አስተናጋጁ እኔን በፕሮግራሙ እንድሳተፍ ጠይቆኝ መጀመርያ እሺ እንዳልኩትና በኋላ ግን ሓሳቤን እንደቀየርኩ አድርጎ ነው ያቀረበው፣ ከሞላ ጎደል ትክክል ነው። ነገር ግን ያልጠቀሰው ነገር ቢኖርና እኔ ያልኩት "በወልቃይት ጉዳይ እንካስላንትያ መግባት አልፈልግም [የዛሬ አምስት ዓመት ምላሽ ሰጥቼበታለሁና]፣ አሁን ኢትዮጵያ ያጋጠማትን ቀውስ ለመወያየት ከሆነ ግን መሳተፍ እፈልጋለሁ" ብዬው ነበር። በተጨማሪም "ከፈለግክ ግን ጥያቄዎች ወደኔ አቅርብና እመልስልሃለሁ፣ ሬኮርድ ማድረግም ትችላለህ" ብዬው ነበር። ይህ ሳይሆን ቀርቶ ግን ከላይ የጠቀስኩትን ፕሮግራም ይዞ ስለቀረበ አንድ ዕድምተኛ የኔን አቋም የሚተች ይዞ ቀረበ። ለነሱ አንገብጋቢ ሆነው ያገኙት የኢትዮጵያ ቀውስና ጦርነት ሳይሆን 'የውልቃይት ጉዳይ' ነው መሰለኝ።

የዛሬ አምስት ዓመት ለዕድምተኛውና ለወልቃይት ድረገፅ እንዲሁም ለሌላ ጥናታዊ ጽሑፍ ያቀረበ ግለሰብ መልስ ሰጥቻቼው ነበር፣ ከዕድምተኛው በስተቀረ ሌሎቹ ሰልጠን ባለ መልኩ ነበር የኔን ሐሳብ የተቃወሙት፣ ለዚሁም አመስግኛቸዋለሁ፣ ዕድምተኛው ግን እሱ ያለው በFacebook ሳይሆን በEthiopian Review ነበር "ውሸታም ፕሮፌሰር" ብሎ የተቸው፣ የቡክን ተራ አራዳ አመለካከት ስለሆነ ደግሞ ለሱ መልስ ሳልሰጥ ለሁለቱ የተጠቀሱትን ነቀፌታዎች ግን መልስ ሰጥቻለሁ። ዕድምተኛው "ሰደበኝ ይላል"፡ "ባራዳስ ያላለውን ይላል"፡ "ስህተቱን ማረም አልፈለገም"፡ "ራስ ጉግሳ አርአያና ራስ ጉግሳ አሌ ለይቶ ማየት አልቻለም" ወዘተ ብሎ ይዘባርቃል። እኔ ጽሑን ያቀረብኩት በሰነድ የተመሮኮዘ ነበር፣ ባራዳስ ብቻ ሳይሆን ሉዶልፍ፡ አልሚዳ፡ ባኪንግሃም የመሳሰሉት ተራኪዎች አቅርብያለሁ፣ በተጨማሪም በአስራሰባተኛው ክፍለዘመን ደጃች ገላውዴዎስ የተባሉ የሽሬ ባላባት ወልቃይት፡ ሰራዊና ሽሬን ጠቅልለው ይገዙ እንደነበር በጽሑፉ አስምሬበታለሁ። ባራዳስ ስለትግራይ መልከአ ምድርና ቆዳ ስፋት ሲያትት

"በምዕራብ እስከ ተከዜ ነው፣ አንዳንድ ሰዎች እንደምያስከብሩት ከሆነ ግን እስከ ሊማሊሞ ነው" ይላል። ይህ እኔ የፈጠርኩት አይደለም፣ ባራዳስ ያለውን ነው ያስቀመጥኩት፣ ካዚህ ቀደም ስለወልቃይት ጉዳይ ካቀረብኳቸው መጣጥፎች ያልጠቀስኩት ዋቢ ምስክር Nubia and Abyssinia by Michael Russell ነው፣ ደራሲው በመጽሐፉ ያማራና የትግራይ ግዛቶች ለይቶ ያስቀምጥና ወልቃይት የትግራይ አድርጎ ነው የሚያስቀምጠው። የወልቃይት ጉዳይ የዛሬ አምስት ዓመት ተቋችቶ ነበር፣ ትምክህተኞቹ ግን አንድን ርእሰ-ነገር መቶ ጊዜ ቢደጋግሙት አይሰለቻቸውም፣ በትግራይ አንድ አባባል አለ፦ "ብውቤ ዝጸመመ ውቤ ክብል ሞተ"፣ ትርጉሙም "በውቤ የደነቆረ (ድዳ የሆነ) ውቤ ሲል ሞተ" ማለት ነው።

አስተናጋጁና ዕድምተኛው ከራስ ውቤ ድዳ ጋር ተመሳሳይነት አላቸው። በነገራችን ላይ፡ ዕድምተኛው ደፋር ብጤ ነው፣ ባስመሳይነት የተካነም ስለሆነ አዋቂ ሆኖ መቅረብ ይፈልጋል እንጂ ገለባነቱ በግልፅ የሚታይ ነው። በአንድ በኩል ግን የሚያስደንቅ አይደለም፣ ምክንያቱም ይብላኝ ለነፍስሔር ፕሮፌሶር ሥርጉው ሃብለስላሴ፣ለታደሰ ታምራት፣ለሪቻርድ ፓንክረስት፣ለተክለፃድቅ መኩርያ፣ለገብሩ ታረቀ፣ለባህሩ ዘውዴ፣ለባይሩ ታፍላ፣ለተወልደ ትኩእ ወዘተ እነዚህ ሊቃውንት እያሉ፡ ዘመኑ የፈጠራቸው የሐሰት ታሪካውያን እንደነ ታየ ቦጋለ (አፄ ዮሐንስን የሚዘልፍ ደንቃራ) ሌሎችም አስመሳዮች እንደ የኢትዮ 360 አስመሳይ ዕድምተኛ በየመድረኩ ሲተቹና ሲሳደቡ የሚውሉት።

ልጅ እናቷን ምጥ ታስተምራለችን? ፍፁም የማይሆን ነገር ነው፣ እነሱ ይደነፉ እንደሆነ እንጂ ምኞታቸውና ፍላጎታቸው ከቶ አይሳካም። ሌላም የማይሳካላቸው ነገር ቢኖር ትንሽ ሆነው ትልቅ ለመሆን መሞከር ነው፣ የተወሰነ እውቀት ኖሯቸው ሊቃውንት ሆነው ለመቅረብ መሻት ወዘተ የባህርይቻው መገለጫ ነው። ለእንዲህ ያለ በራስ ያለመተማመን የሚያንፀባርቁ አብነቶች ላቅርብ፦ ከዕለታት አንድ ቀን በረከት ኪሮስ የሚባል የሥራ ባልደረባየና ጓደኛዬ እንዲህ ብሎ አጫውቶኝ ነበር፦ "በእውቀት ትንሽ የሆነ ሰው ወይም የበታችነት የሚሰማው ሰው ትኩረት ያገኝ ዘንድ ከሱ ታላቅ የሆነውን ሰው ወይ ይነቅፋል፡ አልያም በሐሰት ይወነጅላል"። በተመሳሳይ መልክ ሌላ ጓደኛዬ፡ ፕሮፌሶር ተስፋፅዮን መድሃኔ የሚባል፡ ደግሞ ስለ አንድ እንቁራሪት እንዲህ ብሎ አጫውቶኝ ነበር፦ "ከዕለታት አንድ ቀን እንቁራሪቷ በኩሬ ውሃ እይተንቦራጨቀች እያለች ዝሆን ለመጠጣት ይመጣና በአንኩሮ ተመለከተችው 'በጣም ይገርማል፡ በጣም ግዙፍ እንስሳ ነው፡ እንደሱ መሆን እፈልጋለሁ' አለች፣ 'ምኞት ብቻ ሳይሆን በተግባር ሳይቀር እንደዝሆኑ ለመሆን ሞከረች፣ ራሷን እየነፋች ወይም እያሳበጠች ትንሽነቷን ለመቀየር ሞከረች፣ ተነፋች፡ ተነፋች፡ ተነፋች፣ መጨረሻ ግን ተተኩሳ ሞተች'። የበረከትና የተስፋፅዮን አብነታዊ ጨዋታዎች የኢትዮ 360 አዘጋጅና ዕድምተኛውን በደንብ ይገልጿቸዋል።

**የጠንቋይ ፖለቲካ** የሁለቱ የጸረ-ሕዝብ ኃይሎች አጋር ነው፣ ለብቻው አቅርቦ መተንተን ግን የግድ ይላል። በአዲስ አበባና ዙርያ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን፣ በተለይም የኦርቶዶክስ ኃይማኖት (ሁሉም ባይሆኑም ግን በርካታቻዎቹ) በጠንቋይ ያምናሉ፣ እሁድ እሁድ በቤተክርስትያን ካስቀደሱ በኋላ ወደ ጠንቋይ ቤት የሚሄዱ ቁጥራቸው ብዙ ነው። እንዲህ ያሉ ምእመናን ደግሞ የኋላ ኋላ የገዛ ቤተክርስትያናቸው ነው የሚጎዱት። ይህ ዓይነት ጠንቋይነት ግን አንፃራዊ በሆነ መንገድ ካየነው የሚያስከትለው ጉዳት ቀለል ያለ ነው። በበተክርስትያኑ ይሁን በአገሪቷ ትልቅ ጉዳት የሚያደርሰው ያለው ግን የጠንቋይ ፖለቲካ ነው። የጠንቋይ ፖለቲካ እጅግ መሰሪ የሆነ ጠላት ነው፣ የሃገር ልዑላዊነት አሳልፎ ይሰጣል፣ የሃገር መሬት በሚስጥር ለጎረቤት ሃገር ያስረክባል፣ የኢትዮጵያ መሠረት የሆነውን ትግራይን የውጭ ኃይላትን በመጋበዝ በጦርነት ለመደምሰስ እኩይ ባህርዩን ይተገብራል፣ ጥንታዊ የኢትዮጵያ ቅርሶችና ገዳማት ከሻዕብያ ጋር በመተባበር ያወድማል፣ በትግራይ ህዝብ የዘር ማጥፋት ሴራ በማካሄድ በተግባር ህዝቡ በጅምላ እንዲገደል ያደርጋል፣ ቤንሻንጉል ጉሙዝ ከናካቴው እንዲጠፉ ይፈልጋል፣ በኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ)

ታጋዮች ላይ ጦርነት በማወጅ የኦሮሞን ህዝብ መፍጀት ተቀዳሚ ዓላማው ነው። ይህ የጠንቋይ ፖለቲካ ጽኑ አቋም ነው።

በተጨማሪም የጠንቋይ ፖለቲከኞች ኢትዮጵያ እንድትጠፋ አልያም እጅግ በጣም ደካማና ተመጽዋች ሃገረ-መንግስት (nation-state) እንድትሆን ግዙፍ አጀንዳ ያለው ይመስላል። የጠንቋይ ፖለቲካ አደገኛ ነው፣ በ"ሃገር ፍቅር"፡ "በኃይማኖት ክበር"፡ "በባህል ተቆርቋሪነት" ወዘተ ሊሸፈን ይችላል፣ ሰርጎ የመግባትና የማኮላሸት (ለምሳሌ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሰርገው የገቡ መናፍቃን አሉ) ክዋኔው የላቀ ነው። ከሁሉም የላቀ ግን ከውጭ ሃገር መንግሥታት ሚስጢራዊ ግንኙነቶች በመፍጠር (ለምሳሌ ከሱዲዲ ዓረብያ እና ከዩናትድ አረብ እሚረት) የሃገርን ብሔራዊ ጥቅም ማደብዘዝና ማጥፋት ዋና ተልእኳቸው ነው። ባጭሩ የጠንቋይ ፖለቲካ በሃገር ክህደት (treason) የተሰማሩ እጅግ በጣም አድርባይ የሆኑ ግለሰቦች የሚያስተናግድ እንቅስቃሴ ነው። ብዙውን ጊዜ ደግሞ የጠንቋይ ፖለቲካ ምልአተ ሕዝቡን በውሸት ለማደናገር ይሞክራል፣ የዚሁ ጠባይ ዓይነተኛ ምሳሌ የአብይ አህመድ አማካሪ የሆነውን ድያቆን ተብዬ ዳንኤል ክብረት የአክሱም ፅዮን ዓመታዊ ዝክረ በዓል፡ ማለትም ኅዳር ፳፩ ፡ በመከላከያ ሠራዊት አመካኘነት ፀጥታ ተጠብቆ በከፍተኛ ደረጃ እንደተከበረ መናገሩን በቪድዮ አይተነዋል። ይህ ፍፁም ውሸት ነው፣ በታቃራኒው ኅዳር ፳፩ የአክሱም ፅዮን እንኳንስ ሊከበር ይቅርና በአከባቢው ሰው የሚባል አልነበረም። ባክሱም አከባቢ (በሌላ የትግራይ ከተሞችም ጭምር) ሰው ከቤቱ ከወጣ ስለሚገደል በኅዳር ፳፩ ቀን ሕዝቡ ስለፈራና ከቤቱ ስላልወጣ አከባቢው ጸጥ ረጥ ብሎ ነው የዋለው። ነገር ግን ማርያም ፅዮን ስላልተከበረች ደግሞ ሕዝቡ በከፍተኛ ሃዘን ላይ ወድቆ ነበር።

አብይ አሕመድ የሚያራምደው የጠንቋይ ፖለቲካ ሕዝቡ ልብ አላለም እንጂ ቀደም በሎ በውሸትና በተቃርኖ የተሞላ ነበር። የዛሬ ሦስት ዓመት ኢህአዴግ የመንግሥት ስልጣን ሽግግር ሲያደርግ አብይ አሕመድ ጻድቅ መስሎ ነበር የቀረበው፣ በሕዝቡ ዘንድ ተቀባይነት ለማግኘትም በየክልሉ ዞረ፣ ወደ ትግራይ ሄዶ ሕዝቡን ወርቅ ነህ አለው፣ በኋላ ደግሞ በቦምብ ልደበድብህ ነው ከቤትህ ራቅ አለው፣ ህዝቡ ከቤቱ ራቀ አልራቀ፡ ተጠነቀቀ አልተጠነቀቀ በጅምላ ታጨደ። ወደ አፋር ሂዶ "ኢህአዲግ ደርግን አላቸነፈውም" አለ፣ ለሕዝቡ "እናንተ ኩሽ ናችሁ" አላቸው ማንነታቸውን እንደማያውቁ ሁሉ፣ አሁን ደግሞ በሱማሌ የታጠቁ ኃይሎች አስመታቸው። ወደ ባሌ ተጉዞ ደግሞ "ኦሮሞ መግዛት አይችልም የተባለውን መግዛት እንደሚችል አረጋግጠናል" ብሎ በመመፃደቅ ለኦሮሞ ሕዝብ ጠበቃ ወይም ተቆርቋሪ ሆኖ ነበር የቀረበው፣ አሁን ግን በመሬትና በአየር የኦሮሞን ሕዝብ (በተለይ በምዕራብ ኦሮሚያ) እየጨፈጨፈ እንዳለ የአደባባይ ሚስጢር ነው።

ተቃርኖና ውሸት የአብይ ሁለተኛ የተፈጥሮ ባህርይ (second nature) ሆኗል፣ በዙርያው ያሉ ባለስልጣናትም ተመሳሳይ ባህርይ ነው ያላቸው፣ ሲዋሹም አይታወቃቸውም። እንዲህ ዓይነት በሽታ የተጠ ናወታቸው ግለሰቦች በእንግልዝኛ pathological liars ይባላሉ፣ የቀረበ ያማርኛ ፍቺ 'የሐሰት በሽተኞች' ማለት ነው፣ አያድርስ ነው! ከመዓቱ ይሰውረን የሚያሰኝ ነው! ከሁሉም በላይ የተጎዳቺው ግን ኢትየጵያ ናት፣ አገሪቷ በእንዲህ ዓይነት ከዳተኛ መሪዎች መውደቋ በእጅጉ ያሳዝናል፣ ለመውደቋና ለመታረመሷ ደግሞ የሦስትዮች ጸረ-ሕዝብ ኃይሎች ተጠያቂ ናቸው።

በአሁኑ ዘመን ኢትዮጵያ ወዴት እንደምታመራ ማወቅ አይቻልም፣ ወይ ተበጣጥሳ ታልቃለች፡ ወይ ደግሞ ከማጡና ከድጡ ወጥታ ታንሰራራለች፣ ዳግም ትወለዳለች፡ የኢትዮጵያ ትንሣኤ የሚባል ዘመን የምንመሰክርበት ወቅትም ሊከሰት ይችላል። የኔ ምኞትና ተስፋ ደግሞ ይኸው ነው።

ኢትዮጵያ እንደገና የምታንሰራራ ከሆነች ግን በጀግኖች ልጆቿ አማካኝነት ብቻ ነው ሊሆን የሚችለው። አሁንም ቢሆን ቁጥራቸው ይነስ አንደበታቸው ይታገስ እንጂ በአደባባይ በድፍረት ለህዝባቸውና

ለሃገራቸው የሚቆረቆሩ አልጠፉም። ልደቱ አያሌው፡ በቀለ ገርባ፡ ኢንጂነር ይልቃል፡ ፀጋዬ አራርሳ፡ ህዝቅኤል ጋቢሳ ወዘተ የሚደርጉትን ትግልና መስዋእትነት የኢትዮጵያ ብሩህ ተስፋ የሚያስተጋባ ነው፣ በሚድያ በኩል ደግሞ አዎል ሚድያ (በቃሉ አላምረውና ሃገር ተክለብርሃን)፣ ኢትዮፎረም፣ ዲጂታል ወያነ ደግሞ መጪው ትውልድ ምንጊዜም እየዘከራቸው ይኖራል፣ ለሃገራቸው ያደረጉትን አስተዋፅኦ በሚመለከትም ያስታውሳቿል፡ ያመሰግናቸዋል፡ ያከብራቸዋል።

ይህ በእንዲህ እያለ አራት ኪሎ ላይ አብይና ባልደረበቹ ታላቅ ጠንቋይ ፍለጋ ሽርጉድ ማለት ጀመሩ፣ አስቸኳይ የሦስትዮሽ ስብሰባ ነው፣ የስብሰባው ተካፋዮች ደግሞ አብይ አሕመድ፡ ደመቀ መኮንን፡ ሳህለ–ወርቅ ዘውዴ ናቸው። ስብሰባው የተጠራው ውድቅት ሌሊት ነው፣ ፀጥ ረጥ ብሏል። አጀንዳው ከላይ እንደተጠቀሰው ታላቅ ጠንቋይ ፍለጋ ነው፣ ይህ አፅመታሪክ ወይም የመጪው ጊዜያት ክንውኖች ፍኖተ ካርታ ነው፣ ውጥረት ላይ ነንና ምን እናድርግ ነው። አብይ “እባካችሁ እኔ እንቅልፍ የሚባል ላገኝ አልቻልኩምና ታላቅ ጠንቋይ አግኝታችሁ አገናኙን፡ እንደምታውቁት ሁሉ የአራት ኪሎ ጠንቋይ ብዙ ሥልጣን የለውም” አለ። ደመቀ መኮንን ቀበል አረገና “ከዚህ ቀደም ከሺመልስ አብዲሳ በጨዋታ አንስተነው እርሱ የሚያውቀው ታላቅ የሚባል ከወደ ቢሾፍቱ አለ ብሎኝ ነበር፣ የቢሾፍቱ ጠንቋይ ጋኔን ብጤ ነው አሉ፡ ግን የፈለግነውን ነገር ለማድረግ የሚያዋጣ ይመስለኛል” ካለ በኋላ ሳህለ–ወርቅ ቀጠለችና እኔም ‘እማታቸው ከምሴና ምንጃር የሚገኙ በርካታ ጠንቋዮች አሉ፣ በፍጥነት የሚያሳልጡ ጠንቋዮች ናቸው ሲሉም ሰምቻለሁ፡ ግን አሁን ለምን አስፈለጉ እነዚህ ጠንቋዮች አለች። “እንዴ፡ አልሰማሽም እንዴ” አለ አብይ፡ “ህወሓት እኮ ተመልሶ ወደ ሥልጣን ይመጣል የሚል ወሬ ተነዝቷል” ሳህለ–ወርቅም “በሕልምህ ነው በውንህ?” አለች፣ “አረ በውኔ ነው፣ ቅዠትም ሊሆን ይችላል፡ ምናባቴ ላድርግ” ካለ በኋላ ደመቀ በመቀጠል “ለማንኛውም ጊዜ ሳናጠፋ በፍጥነት በግ ይዘን ወደ ቢሾፍቱ እንሂድ” ካለ በኋላ ሁሉም ወደ ቢሾፍቱ አቀኑ። ጠንቋይ ቤቱ ጋር ደረሱና ታላቁን አገኙት፣ ደህና አድርጎ ተቀበላቸውና “በምን መንገድ ልርዳቹ” አለ በጎራና ድምፅ፣ አብይ በወለሉ የተሰቀሉትን የሳጥናኤልና ሌሎች አጋንንት ስእሎችን እየተመለከተ በመንተባተብ “እኛ'ማ የመጣነው ከቻልክ ጁንታውን እንድታጠፋልን፡ ካልቻልክ ግን ቢያንስ ቢያንስ ወደ ሥልጣን የማይመጡበት ብልሃት እንድትቀይስልን ነበር ወደአንተ የመጣነው” አለ። ደመቀና ሳህለ–ወርቅ አንደበታቸውን ለመክፈት ሲቃጡ፡ ታላቁ “በቃ፡ በቅድምያ አውቅያለሁ ለምን እንደመጣቹ፣ የጠየቃችሁት ካቅሜ በላይ ነው፣ ጁንታ የምትሉትን ደግሞ ማስወገድ አይቻልም፣ ማየት አልቻላችሁም እንጂ ትግራይ በገዳማት የተሞላ መካነ–ፃድቃናት ነው፣ እኛ ጠንቋዮች ከነሱ በላይ መሄድ አንችልም፣ ይልቁንስ አንድ ነገር ልምከራችሁ” ብሎ ጸጥ አለ ለአንድ አምስት ደቂቃ፣ የሦትዮሽ መራሔ–መንግሥት ተደናገጡ። ታላቁ ግን ዝምታውን ጨርሶ በከፍተኛ አንደበት “መጠንቀቅ አለባችሁ፣ አንድ ሁለት የሚሆኑ ከፍተኛ ሹማምንት ይገደላሉ፣ በአዲስ አበባ ነውጥ ይሆናል፣ ከሰሜን ምሥራቅ የሚመጣ ኃይል ማቆም አትችሉም፣ እነ እዜማ እና የትግራይ ዴሞክራቲክ ፓርቲ አይጠቅማችሁም፣ ዕብድ መሳዮች እንደነ ታድዮስ ታንቱ ማስወገድ አለባችሁ። በመጨረሻም የምመክራችሁ ነገር ቢኖር ንሰሐ ገብታችሁ ለእርቀ–ሰላም ተዘጋጅታችሁ በሰላማዊ መንገድ በትግራይ፣ በቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ በኦሮምያ ያሉትን ጦርነቶች አቁሙ፣ አለዛ የሰሜን ምስራቁ ከፊታችሁ ይደቀናል” በማለት አሰናበታቸው።

የኢትዮጵያ ህዋ እንደሚያመላክተው ከሆነ ደግሞ የፈደራሊስት ኃይሎች እንደገና ያንሰራራሉ፣ የብሔር ብሔረሰቦች ዕጣ ፋንታም ከፌዴራል ስርዓቱና ክሕገመንግስቱ ውጪ ሊተገበር አይችልም። መልካም ዕድል ለኢትየጵያ።

**የደራሲውና የአፍሪቃ ልማትና ትምህርት ተቋም (አልትተ) የምርምርና ጥናት መብት በሕግ የተደነገገ ነው። አልትተ ፳፩፫ All Rights Reserved. Intellectual Property Copyright © Institute of Development and Education for Africa (IDEA) 2021**